ኢሰመጉ
EHRCO

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
**ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL**

የምዝገባ ቀፃር
Reg.No. 376

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለህግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡፡
**EHRCO** stands for democracy, the rule of law *and* the respect of human rights.

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ላይ የተፈጸመ የሰብአዊ መብት ጥሰት

## 74ኛ ልዩ መግለጫ

**የካቲት 2 ቀን 1996 ዓ.ም**

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ባሰባሰበው መረጃ ጥር 9 ቀን 1996 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ ውስጥ በሚገኘው የልደት አዳራሽ ከቀኑ 7፡00 ጀምሮ ሊቀርብ የተዘጋጀ የኦሮሞ ተማሪዎች የባህል፣ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ ትርዒት ነበር፡፡ ትርዒቱን እንዲታደሙ ቀደም ሲል በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በተለጠፈ ማስታወቂያ ተጠርተው ከየካምፓሱ የተሰባሰቡ ተማሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው የተለያዩ እንግዶች በአዳራሹ ውስጥ ተገኝተው ነበር፡፡ ዝግጅቱን ከቀኑ 7፡30 ሰዓት ላይ ለመጀመር የትርዒቱ አዘጋጆች ወደ መድረኩ ሲወጡ በአዳራሹ ውስጥ ከተሰበሰቡት ታዳሚዎች መካከል ቲማቲም ተወርውሮባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በአዳራሹ ውስጥ በተሰባሰቡት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና በትርዒቱ አዘጋጆቹ መካከል ግጭት የተፈጠረ ሲሆን ዝግጅቱም በዚህ ምክንያት ተቋርጧል፡፡ የተፈጠረውንም ሁከት ተከትሎ የዝግጅቱ ተጋባዦች ከአዳራሹ ሲወጡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ድንጋይ ይወረወር ነበር፡፡ በድንጋይ ውርወራውም የትርዒቱ ተጋባዥ እንግዶች የመኪና መስታወቶች፣ የልደት አዳራሽና የኬኔዲ ላይብረሪ መስታወቶች እንዲሁም ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ንብረቶች ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ በወቅቱም የተፈጠረውን ግጭት የዩኒቨርሲቲው የጥበቃ ኃይል ለማብረድ ችሏል፡፡ ትርዒቱም በግጭቱ የተነሳ ሳይካሄድ ቀርቷል፡፡ ግጭቱንም ተከትሎ የተከሰተው ሁኔታ ከዚህ በታች በዝርዝር ሠፍሯል፡፡

- ግጭቱ ከበረደ በኋላ ከቀኑ 9፡00 ሰዓት አካባቢ ሲቪል የለበሱ የፀጥታ ኃይሎች ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ 6 ተማሪዎችን በቁጥጥር ስር በማዋል ከልደት አዳራሽ ጀርባ ወስደው በዱላ ደብድበዋቸዋል፡፡ ከዚያም ከግቢው የጥበቃ ኃላፊ ጋር በመሆን ዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ወዳለው ፖሊስ ጣቢያ በመውሰድ እስከ ሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ድረስ በእስር ካቆዩዋቸው በኋላ ወደ አዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ክፍል ተወስደው ታስረዋል፡፡ በዚሁ ዕለት ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ላይ የሲቪል ልብስ የለበሱ የፀጥታ ኃይሉ ወደ ተማሪዎች ማደሪያ ክፍል በማምራት ሌሎች ሁለት ተማሪዎችን ከመኝታቸው አስነስተው በመውሰድ ቀን ከተያዙት ስድስት ተማሪዎች ጋር በአዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ክፍል አስረል፡፡

☎ (00251 1) 56 92 25, 56 48 26, 55 28 14
✉ 2432 Addis Abeba, ETHIOPIA
Telefax: (00251 1) 56 92 27
E-Mail: ehrco@telecom.net.et
Web site: http://www.ehrco.net/

- ኢሰመጉ በአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም ዐቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት አባል እና
- የዓለም ዐቀፍ የሰብአዊ መብቶች ፌዴሬሽን ኮረስፖንዲንግ አባልም ነው፡፡
- EHRCO has an observer status in the African Commission on Human and People's Rights, is a member of World Organization Against Torture and is also a corresponding member of the International Federation of Human Rights.

ሠንጠረዥ 1. ጥር 9/1996 ዓ.ም ተይዘው በአ.አ ወንጀል ምርመራ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች

| ተ/ቁ | የተማሪው ሙሉ ስም | ካምፓስ | የትምህርቱ ዘርፍ |
|---|---|---|---|
| 1 | እምሩ ገመቹ | 6 ኪሎ | ፖለቲካል ሳይንስ |
| 2 | ጌታቸው ጋዲሣ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን |
| 3 | በሊና ሞንቆቻ | " | " " |
| 4 | ታምራት ጋዲሣ | " | " " |
| 5 | ትርፌሳ በርኬሳ | " | አካውንቲግ |
| 6 | ተመስገን ገመዳ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን |
| 7 | መርጋ ነሞ | " | ሳይኮሎጂ |
| 8 | ሚሊዮን ዲሪባ | " | ማኔጅመንት |

ከላይ ስማቸው ከተጠቀሱት 8 ተማሪዎች መካከል በተ/ቁ 1 ላይ ስሙ የተጠቀሰውን ተማሪ እምሩ ገመቹን የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ዲን ከሌሊቱ 9:00 አካባቢ ከተኛበት ክፍል ድረስ በመሄድ ልናነጋግርህ እንፈልጋለን ብለው የቀሰቀሱት መሆኑንና ቢሮአቸው ከወሰዱት በኋላም ለጸጥታ ሀይሎች አሳልፈው ሰጥተውታል፡፡

- ይህንን ሁኔታ የተመለከቱ ሌሎች ተማሪዎች ጥር 10 ቀን 1996 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ዲን ቢሮ በመሰባሰብ ስምንቱ ተማሪዎች ለምን እንደተያዙና በወቅቱ የሚገኙበትንም ሁኔታ እንዲያሳውቋቸው፣ ዲኑ ተማሪ እምሩ ገመቹን ለምን ከተኛበት ቀስቅሰው ለፖሊስ አሳልፈው እንደሰጡት እና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙት የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ለደህንነታቸው የሰጉ መሆኑን ገልጸው ለደኅንነታቸው ዋስትና እንዲሰጣቸው የጠየቋቸው መሆኑን ተማሪዎች ገልጸዋል፡፡
- የተማሪዎቹ ዲንም ተማሪ እምሩን ሊያነጋግሩት ሲወስዱት ፖሊሶች ከመንገድ ላይ የተረከቧቸው መሆኑን ከገለጹላቸው በኋላ የተያዙት ስምንቱ ተማሪዎች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ የተወሰኑ ተማሪዎች ተወክለው ከታሰሩበት ሥፍራ ድረስ ሄደው ለማየት የሚችሉ መሆናቸውን እንዳሳወቋቸው ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡
- በዚህም መሠረት የተወከሉ አምስት ተማሪዎች ጥር 10 ቀን 1996 ዓ.ም አዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ክፍል በመሄድ የታሰሩትን 8 ተማሪዎች ካነጋገሩ በኋላ ወደ ዩኒቨርስቲው ተመልሰው ይጠብቋቸው ለነበሩት ተማሪዎችና ለዲኑ ታሳሪዎቹ በደህና ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ ለቀሪ ጥያቄዎቻቸውም ምላሽ እንዲሰጣቸው ዲኑን የጠየቁ ሲሆን ኃላፊውም ተማሪዎቹ ላነሱዋቸው ቀሪ ጥያቄዎች ጥር 12 ቀን 1996 ዓ.ም ከቀኑ በ6.00 ሰዓት ላይ ምላሽ የሚሰጧቸው መሆኑን ገልጸው የሸኟቸው መሆኑን ተማሪዎቹ ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡
- ጥር 11 ቀን 1996 ዓ.ም. ከምሽቱ 3:00 አካባቢ ስድስት ኪሎ ካምፓስ ውስጥ መብራት የተቋረጠ ሲሆን ይሄንኑ ተከትሎ አሁን የዩኒቨርሲቲው የ1ኛ ዓመት ተማሪዎች ማደሪያ የሆነውና በተለምዶ "ሳይቤሪያ" ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ወደ ሕንጻ ቁጥር 505 ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች ድንጋይ በመወርወሩ መስታወቶች መሰባበራቸውን፣ ወዲያውኑም የፌዴራል ፖሊስ ኃይሎች የመኪናቸውን መብራት በማጥፋት በጭለማ ውስጥ ወደ ተማሪዎቹ ማደሪያ ሄደው ዘጠኝ ተማሪዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰባቱን ለቀው ሁለት የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎችን ይዘዋቸው የሄዱ መሆኑን የአይን እማኞች ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡
- ጥር 12 ቀን 1996 ዓ.ም ከቀኑ 6:00 ሰዓት ላይ የዲኑን ምላሽ ለማግኘት ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ቢሮ ፊት ለፊት በርካታ ተማሪዎች ተሰባስበው ሲጠባበቁ የቆዩ ቢሆንም ዲኑ በሥፍራው ሳይገኙ ቀርተዋል፡፡ ይሁንና

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት ከቀኑ 8:00 ሰዓት አካባቢ ወደ ተሰባሰቡት ተማሪዎች በመምጣት ለምን እንደተሰባሰቡ ተማሪዎቹን ጠይቀዋቸዋል። ተማሪዎቹም ዲኑ በሰጡዋቸው ቀጠሮ መሠረት ምላሽ ለማግኘት የተሰባሰቡ መሆኑን ገልጸዋል። የዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎችም ተማሪዎቹ ጉዳያቸው በፍ/ቤት እየታየ መሆኑን በመግለጽ በአስቸኳይ እንዲበተኑ በማስጠንቀቅ የማይበተኑ ከሆነ ከውጪ የፖሊስ ኃይል የሚጠሩ መሆኑን ገልጸው ወደ ቢሮዋቸው የተመለሱ መሆኑን ተማሪዎቹ ለኢሰመጉ ገልጸዋል።

- ከቀኑ 9:00 ሰዓት ላይም በመቶዎች የሚቆጠሩ የፌዴራል ፖሊስ ሠራዊት አባላት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲው መግቢያ በሮች ተሰልፈው በመግባት መሣሪያ የታጠቁት ግቢውን ሲከቡ ዱላና የድንጋይ መከላከያ ሄልሜት ያጠለቁት ፖሊሶች ደግሞ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ቢሮ ፊት ለፊት የተሰበሰቡትን ተማሪዎች ከበዋቸዋል።
- በመቀጠልም የተሰበሰቡት ተማሪዎች በሙሉ መታወቂያቸውን እንዲያስረክቡ ተደርጎ ሴት ተማሪዎችን በአንድ መኪና ወንዶቹን ደግሞ በሌሎች የፖሊስ ካሚዮኖች በመጫን ወደ ኮልፌ የፖሊስ ማሰልጠኛ ካምፕ መውሰዳቸውን ለኢሰመጉ ገልጸዋል።
- በማሰልጠኛ ካምፑ እንደደረሱ እያንዳንዱ ተማሪ ስሙ፣ የመኖሪያ አድራሻውና የትምህርት ክፍሉ (ዲፓርትመንት) የተመዘገበ ሲሆን ቀበቷቸውን እንዲፈቱና ጫማቸውን አውልቀው በባዶ እግራቸው እንዲሆኑ ተደርገዋል። ከዚያም ከ10:00 እስከ ምሽቱ 1:30 ሰዓት ድረስ ተማሪዎቹ በባዶ እግራቸው በጠጠር ላይ እንዲሮጡ፣ ልብሳቸውን ከጉልበታቸውና ከክርኖቻቸው በላይ ሰብስበው በእንብርክካቸውና በእጆቻቸው መዳፍ እየተንፏቀቁ ኮረታማ ቀይ አሸዋ በተነጠፈበት ሜዳ ላይ እንዲመላለሱ፣ በሜዳው ላይ በጀርባቸው እንዲንከባለሉ፣ አንዱ ተማሪ ሌላውን እያዘለ በጠጠሩ ላይ እንዲሮጡ በማድረግ እስከ ምሽቱ 1:30 ሰዓት ድረስ የማሰቃየት ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል።
- ከምሽቱ 1:30 ሰዓት በኋላም ተማሪዎቹ እንዲሰለፉ ተደርጎ በካምፑ ውስጥ በሚገኙ አምስት አዳራሾች ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል። በሦስቱ አዳራሾች በእያንዳንዳቸው ቁጥራቸው 120 የሚደርሱ ወንድ ተማሪዎች እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን በአንደኛው ክፍል ደግሞ 103 ወንዶች ታስረዋል። 31 ሴት ተማሪዎችም ለብቻቸው በአንድ አዳራሽ ውስጥ ታስረዋል። በያሉበትም ክፍል ውስጥ ለእያንዳንዱ ተማሪ አንዳንድ ደረቅ ዳቦ ተሰጥቶታል።
- ተማሪዎቹ ሌሊቱን ቀዝቃዛ የሲሚንቶ ወለል ላይ እንዲተኙ ተደርገዋል። ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት ላይም ሴቶቹ ካሉበት ክፍል በቅድሚያ እንዲወጡ ተደርገው ከላይ በተገለጸው መልኩ የማሰቃየት ተግባር ተፈጽሞባቸዋል። ስቃዩን መቋቋም ያቃታቸው ሴቶች ያለቅሱ የነበረ ሲሆን በፖሊሶቹም ተደብድበዋል። ወንዶቹንም ከሌሊቱ 10:30 ሰዓት ላይ ካሉበት ክፍል በማውጣት እስከ ጠዋቱ 2:00 ድረስ ሲያሰቃዩዋቸው ቆይተው መልሰው በየክፍሉ አስገብተዋቸዋል።
- ጥር 13 ቀን 1996 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ላይ ለተማሪዎቹ በያሉበት ክፍል አንዳንድ ደረቅ ዳቦ ተሰጥቷቸዋል። ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ላይ እያንዳንዱ ተማሪ እየተጠራ የመኖሪያ አድራሻውን እንዲያስመዘግብ ከተደረገ በኋላ ጥፋተኛ መሆናችሁን ታምናላችሁ ወይ? የሚል ጥያቄ በመርማሪ ፖሊሶች የቀረበላቸው ሲሆን ሁሉም ተማሪ "ጥፋተኛ አይደለሁም" የሚል ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷቸዋል። ከዚያም አሥር አሥር ተማሪዎች በአንድ ላይ እንዲሆኑ ተደርጎ ፎቶ ግራፍ የተነሱ ሲሆን በቪዲዮ ካሜራም ተቀርጸዋል።
- ከተማሪዎቹም መካከል ሁለት ሴቶችና አሥራ ሁለት ወንዶች ተለይተው ወደ አዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል ተወስደዋል። ለተቀሩትም ተማሪዎች

ከዚህ በኋላ ዩኒቨርሲቲው አካባቢ ቢገኙ የከፋ ቅጣት እንደሚጠብቃቸውና ትምህርታቸውን የመቀጠላቸውንም ሁኔታ በተመለከተ ማታ በሬዲዮና በቴሌቪዥን መግለጫ እንዲከታተሉ ተገልጾላቸው ለአራት ተማሪዎች አንድ ፖሊስ እየተመደበ በተለያዩ የማሰልጠኛ ካምፑ መውጫ መንገዶች በእግራቸው እንዲወጡ ተደርገው ተለቀዋል::

- ተማሪዎቹ ከኮልፌ የፖሊስ ማሰልጠኛ ካምፕ በእግራቸው ተጉዘው ወደ ዩኒቨርሲቲው አካባቢ የተመለሱ ቢሆንም በፖሊሶቹ የተወሰደባቸው መታወቂያ ስላልተመለሰላቸው ወደ ዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ለመግባት አልቻሉም:: አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከአዲስ አበባ ውጭ ካሉ አካባቢዎች የመጡ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ የመጠለያና የምግብ ችግር ገጥሟቸዋል:: በተጨማሪም ወደ ዩኒቨርሲቲው ለመግባት ባለመቻላቸው ከመኝታ ክፍላቸው ውስጥ ቅያሪ ልብሶቻቸውንና የመማሪያ መሳሪያዎቻቸውን ለመውሰድ አልቻሉም:: ተማሪዎቹ በአሁኑ ወቅት ምግባቸውን እየለመኑ እንደሚመገቡና አዳራቸውም በየበረንዳው እንደሆነ ለኢሰመጉ ገልጸዋል::
- ተማሪዎቹ ወደ ትውልድ ቀያቸውም እንዳይመለሱ ስጋት ያደረባቸው መሆኑን ገልጸዋል:: የስጋታቸው ምክንያትም የስም ዝርዝራቸው ለመጡበት ክልል ፖሊስ የተላከ ስለመሆኑ ለአንዳንዶቹ ከቤተሰቦቻቸው መልዕክት የደረሳቸው መሆኑና ወደ መኖሪያቸው ቢመለሱ ከዚህ የከፋ ችግር ሊደርስባቸው እንደሚችል በመገመታቸው ነው::

ሠንጠረዥ 2. ከኮልፌ ፖሊስ ማሰልጠኛ ካምፕ ወደ አ.አ ወንጀል ምርመራ ክፍል ተወስደው የታሰሩ

| ተ/ቁ | የተማሪዎቹ ሙሉ ስም | ካምፓስ | የትምህርቱ ዘርፍ |
|---|---|---|---|
| 1 | መሰለች ታደሰ | 6 ኪሎ | የፖለቲካል ሳይንስ |
| 2 | ለሊሴ ታደሰ | " | የቢዝነስ ኤዱኬሽን |
| 3 | ወርቁ በንቲ | " | የእንግሊዘኛ ቋንቋ |
| 4 | ጋዲሣ መርጋ | " | የኢንፎርሜሽን |
| 5 | ሀብታሙ ጅማ | " | የእንግሊዘኛ ቋንቋ |
| 6 | አሚኒ አብዱልከሪም | " | የሕግ |
| 7 | ደሳለኝ ለገሠ | " | የእንግሊዘኛ ቋንቋ |
| 8 | ታዬ ደንደአ | " | የሕግ ተማሪ |
| 9 | ሐሰን ባሪሶ | " | የታሪክ ተማሪ |
| 10 | ዳዊት ኩዳ | " | ሕግ |
| 11 | ብርሃኑ መኮንን | 4 ኪሎ | ባዮሎጂ |
| 12 | ተሊላ ቡልቡላ | 5 ኪሎ | ኢንጂነሪንግ |
| 13 | ገመቺስ ኃይሌ | 5 ኪሎ | ፋርማሲ |
| 14 | ቶሎሣ አበላ | 5 ኪሎ | ፋርማሲ |
| 15 | ሚልኬሣ ደንደአ | 5 ኪሎ | ኢንፎርሜሽን ሳይንስ |

የፌዴራል ፖሊስ ጥር 12 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተፈጠረ ሁከት ንብረት አውድመዋል ያላቸውንና በሁከቱ ተሳትፈዋል የተባሉ 329 ተማሪዎችን በቁጥጥር ስር ያዋለ መሆኑን ገልጿል:: በተጨማሪም የፌዴራል ፖሊስ ጥር 13 ቀን ባወጣው መግለጫ በቁጥጥር ስር ካዋላቸው 329 ተማሪዎች መካከል 315 የሚሆኑትን ለቆ 14 ተማሪዎችን ግን ለፍርድ ለማቅረብ ምርመራውን እያካሄደ እንደሆነ ገልጿል:: የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጽ/ቤትም በዚሁ ዕለት ባወጣው መግለጫ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋሉት ተማሪዎች መካከል 315 የሚሆኑትን ለ1 ዓመት ከትምህርታቸው ያገዳቸው መሆኑንና ተማሪዎቹ በቀጣዩ ዓመት በመልሶ ቅበላ ኮሚቴ ፊት ጥፋታቸውን ካመኑ ወደ ትምህርት ገበታቸው እንደሚመለሱ

ገልጿል፡፡ ቀሪዎቹ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተካሄደባቸው ያሉትን ተማሪዎች ግን ዩኒቨርሲቲው ሙሉ በሙሉ ያባረራቸው መሆኑን ገልጿል፡፡

ኢሰመጉ ታስረው ከነበሩት ተማሪዎች ያገኘው መረጃ የሚያመለክተው ቁጥራቸው 494 የሚጠጉ ተማሪዎች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው ድብደባና እንግልት የተፈጸመባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ማሰባሰብ የተቻለው የ349 ተማሪዎችን የሥም ዝርዝር ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች የተበታተኑ በመሆኑና መሰባሰብ ባለመቻላቸው የሁሉንም ተማሪዎች የስም ዝርዝር ለማግኘት አልተቻለም፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ጥር 9 ቀን 1996 ዓ.ም ስምንት ተማሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሎ ጥር 10/1996 ዓ.ም ፍርድ ቤት ያቀረባቸው መሆኑን ለኢሰመጉ የገለጸ ሲሆን በእስር ላይ የሚገኙትን ተማሪዎችም በግንባር ቀርቦ ለመጎብኘት ተችሏል፡፡ ፖሊስ በስምንቱ ተማሪዎች ላይ የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ የሚገኘው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት የፈቀደለት ሲሆን ለጥር 24 ቀን 1996 ዓ.ም እስረኞቹን ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ፖሊስም በቀጠሮው ዕለት ተማሪዎቹን ፍ/ቤት ይዞ በመቅረብ ተጨማሪ የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ተፈቅዶለታል፡፡ ጥር 12 ቀን 1996 ዓ.ም በፌዴራል ፖሊስ ከተያዙት ተማሪዎች መካከል ተለይተው ጥር 13 ቀን 1996 ዓ.ም ከኮልፌ ፖሊስ ማሰልጠኛ ወደ አዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል የተወሰዱት 15 ተማሪዎች ጥር 14 ቀን 1996 ዓ.ም ሚክሲኮ አደባባይ አካባቢ የሚገኘው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት ቀርበዋል፡፡ ፖሊስም የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት ፍ/ቤቱ የፈቀደለት ሲሆን ተማሪዎቹን ለጥር 28 ቀን 1996 ዓ.ም ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ኢሰመጉም ሂደቱን በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 1 እና 2 ላይ ሥማቸው የተጠቀሰው 23 ተማሪዎች ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ክፍል ቁጥጥር ስር ይገኛሉ፡፡

ኢሰመጉ በደል የተፈጸመባቸው ተማሪዎች ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ስለሁኔታው የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚደንት ለማነጋገር ጽ/ቤታቸው ድረስ በግንባር በመሄድና ስልክ በመደወል ሙከራ አድርጓል፡፡ ጥር 24 ቀን 1996 ዓ.ም ፕሬዚዳንቱን ለማነጋገር ለጽ/ቤታቸው ኢሰመጉ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ለየካቲት 1 ቀን 1996 ዓ.ም በፀሐፊያቸው በኩል ቀጠሮ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ጥር 28 ቀን 1996 ዓ.ም ከፕሬዚደንቱ ጽ/ቤት ለኢሰመጉ ስልክ ተደውሎ ፕሬዚዳንቱ በቀጠሮው ዕለት ኢሰመጉን ለማነጋገር እንደማይችሉና ቀጠሮውም የተሰረዘ መሆኑን ተነግሯል፡፡ በዚህም ምክንያት በተማሪዎቹ ላይ ስለተወሰደው እርምጃ የዩኒቨርሲቲውን ሃሳብ በዚህ መግለጫ ላይ ማካተት አልተቻለም፡፡

ሠንጠረዥ 3. ኮልፌ ፖሊስ ማሠልጠኛ ካምፕ ውስጥ በእስር ቆይተው የተለቀቁ ተማሪዎች

| ተ/ቁ | የተማሪው ሙሉ ስም | ጾታ | ዲፓርትመንት | ዓመት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አብዲ በቀለ | ወንድ | የህዝብ አስተዳደር | 3ኛ |
| 2 | አብዲ ነመራ | " | ፋርማሲ | 3ኛ |
| 3 | አብዲሹ አደም | " | ፕሪ ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |
| 4 | አብዱላዚቅ ሁሴን | " | ፋርማሲ | 3ኛ |
| 5 | አብዱልሀኪም | " | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 6 | አብዱልከድር ዋሊይ | " | ፋርማሲ | 3ኛ |
| 7 | አብዱልዘረቅ ሁሴን | " | " | 3ኛ |
| 8 | አበባዬ በቀለ | ሴት | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 9 | አበበ አብደታ | ወንድ | ቢዝነስ ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 10 | አበበ በየነ | " | ፕሪ ኢንጂነሪንግ | 2ኛ |
| 11 | አበራ ብርሃኑ | " | ፋርማሲ | 3ኛ |
| 12 | አበራ መንገሻ | " | ፕሪ ኢንጂነሪንግ | 2ኛ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13 | አብርሃም ምትኩ | " | ሕግ | 2ኛ |
| 14 | አብዮት ደስታ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 4ኛ |
| 15 | አዳነ ሲሳይ | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 16 | አዲሱ አቶምሳ | " | ፋርማሲ | 3ኛ |
| 17 | አዱኛ ነጋሳ | " | ፊዚክስ | 2ኛ |
| 18 | አህመድ አማን | " | ኬሚካል ኢንጂነሪን | 3ኛ |
| 19 | አህመድ መሃመድ | " | ማኔጅመንት | 2ኛ |
| 20 | አህመድ መሃመድ | " | ጆግራፊ | 2ኛ |
| 21 | አጀማ በቀለ | " | ፋርማሲ | 4ኛ |
| 22 | አለም ደምሴ | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 23 | አለማየሁ አብዲሣ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 24 | አለማየሁ ቦሩ | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 25 | አለማየሁ ገርባ | " | ጆግራፊ | 4ኛ |
| 26 | አለማየሁ ጉርሜሳ | " | ኢኮኖሚክስ | 3ኛ |
| 27 | አለማየሁ ጉርሜሳ | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 28 | አለሙ ኃይሌ | " | ፕሪ ኢንጂነሪንግ | 2ኛ |
| 29 | አለሙ ኢጀራ | " | ሕግ | 2ኛ |
| 30 | አለሙ ሙለታ | " | ቢዝነስ ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 31 | አለሙ ሮሬሳ | " | ጆግራፊ | 3ኛ |
| 32 | አለሙ ሮሬሳ | " | ሒሳብ | 4ኛ |
| 33 | አሊ ታዲ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 34 | አሊይ ደሲዮ | " | " | 3ኛ |
| 35 | አማኑኤል ተመስገን | " | አማርኛ | 2ኛ |
| 36 | አመኑ ዳባ | " | ኮሜርስ | 2ኛ |
| 37 | አመኑ ሁንዴ | " | ፊዚካል | 3ኛ |
| 38 | አመኑ ሴንጂ | " | " | 4ኛ |
| 39 | አመዩ ቶላ | " | ሶሻል ሳይንስ | 2ኛ |
| 40 | አሚን መሐመድ | " | ፊሎዞፊ | 2ኛ |
| 41 | አሪፍ አብዱላሂ | " | " | 3ኛ |
| 42 | አሰፋ ቶሎሳ | " | ህዝብ አስተዳደር | 2ኛ |
| 43 | አሰፋ ያደታ | " | ጆግራፊ | 2ኛ |
| 44 | አሰፋ ገርቢ | " | ባይሎጂ | 4ኛ |
| 45 | አስፋው ዱጉማ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 46 | አሻግሬ ገ/ወልድ | " | ሕግ | 3ኛ |
| 47 | አሸናፊ በንቲ | " | ህክምና | 3ኛ |
| 48 | አያንሳ አብዲሳ | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 49 | አያንሳ ፋንታ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 50 | አያንቱ ባጫ | ሴት | ሕግ | 3ኛ |
| 51 | አያንቱ ያደጨ | " | ኮንፒዩተር ሳይንስ | 3ኛ |
| 52 | ባንጃው በቀለ | ወንድ | ኢንፎርሜሽን ሳይንስ | 4ኛ |
| 53 | በንቲ ፊሮምሳ | " | ፋርማሲ | 2ኛ |
| 54 | በረካ ዶሪ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 55 | ባይሳ ደሬሳ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 56 | ባይሳ ለታ | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 57 | በዳሣ በቀለ | " | ሒስትሪ | 2ኛ |
| 58 | ቤኛ ጫላ | " | መካኒካል ኢንጅነሪንግ | 3ኛ |
| 59 | በቀማ ያነዶ | " | ኬሚስትሪ | 3ኛ |
| 60 | በክሪ ገመቹ | " | ጆግራፊ | 2ኛ |
| 61 | በላይ ተሰማ | " | ቢዝነስ ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 62 | በላይ ሙለታ | " | ሊንጉስቲክ | 2ኛ |
| 63 | በላይ ተክሌ | " | ጆግራፊ | 2ኛ |
| 64 | በሪሁን አራርሳ | " | " | 3ኛ |
| 65 | ባይሣ ዴንሳ | " | ሕግ | 2ኛ |
| 66 | ቢፋ ተሊላ | " | እንግሊዘኛ | 3ኛ |
| 67 | ቢቂላ | " | አማርኛ | 2ኛ |
| 68 | ቢቂላ ሀምቢሁን | " | ቢዝነስ ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 69 | ቢሊሱማ ደብሬ | " | አርክቴክቸር | 5ኛ |
| 70 | ብርሃን መርጋ | ሴት | ሊንጉስቲክ | 2ኛ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 71 | ብርሃኑ ቦጋለ | ወንድ | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 72 | ብርሃኑ መላኩ | " | ኢኮኖሚክስ | 3ኛ |
| 73 | ብርሃኑ ያደታ | " | ኬሚስትሪ | 2ኛ |
| 74 | ብርሃኑ ገመቹ | " | እንግሊዝ | 3ኛ |
| 75 | ቦጋለ ሽፈራሁ | " | ፕሪ ኢንጂነሪንግ | 3ኛ |
| 76 | ቦኬሺ | ሴት | " | 3ኛ |
| 77 | ቦንቱ ተሾመ | ወንድ | ቴክኖሎጂ | 2ኛ |
| 78 | ቡላ ዋካሳ | " | ጆግራፊ | 3ኛ |
| 79 | ቡርካ ናኔሳ | " | ቢዝነስ ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 80 | ጫላ ደቻሳ | " | " | 2ኛ |
| 81 | ጫላ ዲሣሣ | " | ህዝብ አስተዳደር | 2ኛ |
| 82 | ጫልቱ አለሙ | ሴት | ኢንፎርሜሽን ሳይንስ | 2ኛ |
| 83 | ጫልቱ ታከለ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 2ኛ |
| 84 | ጫልቱ ተስፋዬ | " | ቢዝነስ ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 85 | ጫልቺሳ ደብሪ | ወንድ | አስተዳደር | 2ኛ |
| 86 | ጨርቃ ኮርማ | " | ጆግራፊ | 2ኛ |
| 87 | ጭምዲ ዲንኪ | " | መካኒካል ኢንጂነሪንግ | 4ኛ |
| 88 | ጩቼ ፋንታ | ሴት | " | 5ኛ |
| 89 | ዳግም ገዳ | ወንድ | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 90 | ዳመነ አበበ | " | አስተዳደር | 2ኛ |
| 91 | ደሜ ታዬ | " | ኮንፒዩተር ሳይንስ | 3ኛ |
| 92 | ዳንኤል አምቢሳ | " | " | 3ኛ |
| 93 | ዳንኤል በቀለ | " | " | 3ኛ |
| 94 | ዳንኤል ገመቹ | " | ፋርማሲ | 5ኛ |
| 95 | ዳንኤል ለታ | " | እንግሊዘኛ | 3ኛ |
| 96 | ዳኛቸው ኃ/ማርያም | " | " | 4ኛ |
| 97 | ዳዊት ቡሊ | " | ሲቪል ኢንጂነሪንግ | 4ኛ |
| 98 | ደበሌ ጌታቸው | " | ኬሚስትሪ | 2ኛ |
| 99 | ደቻሳ መርጋ | " | እንግሊዘኛ | 3ኛ |
| 100 | ደቻሳ ደሬሳ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 101 | ደቻሳ ገለታ | " | ሊንጉስቲክስ | 3ኛ |
| 102 | ደገፉ ሙሉጌታ | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 103 | ደጊቱ ዴንሳ | ሴት | ህዝብ አስተዳደር | 2ኛ |
| 104 | ደጉ ደምሴ | ወንድ | ሒስትሪ | 2ኛ |
| 105 | ደጀኔ ቦሩ | " | ፕሪ ኢንጂነሪንግ | 2ኛ |
| 106 | ደጀኔ ተክሌ | " | " | 2ኛ |
| 107 | ደጀኔ ጸጋዬ | " | ኬሚስትሪ | 3ኛ |
| 108 | ደጀኔ ወ/ሰማያት | " | " | 4ኛ |
| 109 | ደጀኔ ዋቅቶላ | " | እስታትስቲክ | 3ኛ |
| 110 | ደንገ ለገሰ | " | አስተዳደር | 3ኛ |
| 111 | ደራርቱ ኃይሌ | " | ፋርማሲ | 2ኛ |
| 112 | ደረጄ ጨመዳ | " | " | 4ኛ |
| 113 | ደረጄ ጉተታ | " | ሶሻል ሳይንስ | 4ኛ |
| 114 | ደረጄ ከበደ | " | ጂኦሎጂ | 2ኛ |
| 115 | ደረጄ ምስጋኔ | " | ሶሻል ሳይንስ | 2ኛ |
| 116 | ደረጄ ተሎ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 117 | ደረጄ ዋቅቶላ | " | እስታትስቲክ | 3ኛ |
| 118 | ደረሱ አበራ | " | እንግሊዘኛ | 4ኛ |
| 119 | ደረጄ ከሎ | " | " | 3ኛ |
| 120 | ደሳለኝ ጎሹ | " | " | 3ኛ |
| 121 | ደሳለኝ ተረፈ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 122 | ደስታ ቶሌራ | " | ሲቪል ኢንጂነሪንግ | 5ኛ |
| 123 | ዳንጌ ቦሩ | " | ፋርማሲ | 3ኛ |
| 124 | ዲንሳ ለሜሳ | " | | |
| 125 | ድሪባ ግርማ | " | ሒስትሪ | 3ኛ |
| 126 | ድሪባ ማዴሳ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 127 | ዲሣሣ ቶሌራ | " | ፋርማሲ | 5ኛ |
| 128 | ዱላ ዋቃሳ | " | ጆግራፊ | 3ኛ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 129 | ኤቢሳ አላና | " | ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ | 5ኛ |
| 130 | እጅጉ ጋሻ | " | አማርኛ | 4ኛ |
| 131 | እስክንድር አልዬ | " | ኬሚስትሪ | 4ኛ |
| 132 | ፋንታ ፍቃዱ | " | ፊሎዞፊ | 2ኛ |
| 133 | ፍቃዱ ዲሣሣ | " | ሶሻል ሳይንስ | 2ኛ |
| 134 | ፊይሣ ቢጂጋ | " | " | 4ኛ |
| 135 | ፉአድ ሐምዛ | " | ፊዚክስ | 3ኛ |
| 136 | ፎዚያ አህመድ | ሴት | ቲያትሪካል አርት | 2ኛ |
| 137 | ገዳ ጀምበሬ | ወንድ | እንግሊዘኛ | 3ኛ |
| 138 | ገዳ ቶሌራ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 139 | ጋዲሣ ሒርጳሳ | " | ሲቪል ኢንጂነሪንግ | 4ኛ |
| 140 | ጋዲሴ ተሰማ | ሴት | ቴክኖሎጂ | 3ኛ |
| 141 | ገልገሎ ሐለቀ | ወንድ | ማኔጅመንት | 2ኛ |
| 142 | ጋሩማ ሰኚ | " | ሒሳብ | 4ኛ |
| 143 | ገዛሐኝ እንድሪስ | " | አካውንቲንግ | 2ኛ |
| 144 | ገብሬ ሁሉቃ | " | አማርኛ | 3ኛ |
| 145 | ገመቺስ በቀለ | " | ፋርማሲ | 4ኛ |
| 146 | ገመቺስ መርጋ | " | ኬሚስትሪ | 2ኛ |
| 147 | ገመቺስ ሞሲሳ | " | ሶሻል ሳይንስ | 3ኛ |
| 148 | ገመቹ ደሬሳ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 149 | ገመቹ ጊቤ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 150 | ገመቹ ተርፋሳ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 151 | ገመቹ ናፋባስ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 152 | ገናሞ ባሪሶ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 3ኛ |
| 153 | ጌታቸው አሰፋ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 2ኛ |
| 154 | ጌቴ ቀነአ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 2ኛ |
| 155 | ጌቱ አባተ | " | ሲቪል ኢንጂነሪንግ | 4ኛ |
| 156 | ጌቱ ተረፈ | " | ሲቪል ኢንጂነሪንግ | 4ኛ |
| 157 | ግርማ ባህሩ | " | አካውንቲንግ | 2ኛ |
| 158 | ግርማ ደሳለኝ | " | " | 2ኛ |
| 159 | ግርማ ተመስገን | " | " | 2ኛ |
| 160 | ግዛቸው ጋቢሳ | " | " | 2ኛ |
| 161 | ጉርሜሳ መርጋ | " | ፊሎሶፊ | 2ኛ |
| 162 | ጉያ ታፈሰ | " | " | 2ኛ |
| 163 | ሐቢብ ድሪስ | " | ፊዚክስ | 2ኛ |
| 164 | ሐቢብ ፉሮ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 165 | ሐብሩዲ ቶላ | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 166 | ሐብታሙ አቦማ | " | ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ | 3ኛ |
| 167 | ሐብታሙ ፈይሳ | " | ፊዚካል ኤዱኬሽን | 2ኛ |
| 168 | ሐብታሙ መንግሥቱ | " | " | 4ኛ |
| 169 | ሐብታሙ ታደሰ | " | " | 4ኛ |
| 170 | ሐብቱ ጅማ | " | ፕሪ ኢንጂነሪንግ | 2ኛ |
| 171 | ሐሰን መሐመድ | " | " | 4ኛ |
| 172 | ሃሰን ሹቤ | ወንድ | ጂኦሎጂ | 2ኛ |
| 173 | ሃዊኒ በንቲ | ሴት | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 174 | ሃዊሶ ደጊ | ወንድ | ቴክኖሎጂ | 3ኛ |
| 175 | ሃያታ ደልቻ | " | ኬምስትሪ | 2ኛ |
| 176 | ሃይደር አማን | " | አማርኛ | 3ኛ |
| 177 | ሂካ ፈቀደ | " | እንግሊኛ | 4ኛ |
| 178 | ሂካ ጉተማ | " | ሶሲዮሎጂ | 3ኛ |
| 179 | ሁሴን ቡሎ | " | " | 4ኛ |
| 180 | ሁሴን ጉዮ | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 181 | ኢብሳ ደጀኔ | " | ፊሎዞፊ | 2ኛ |
| 182 | ኢብሳ ሰርቤሳ | " | " | 3ኛ |
| 183 | እናትትሁን ፉፋ | ሴት | ታሪክ | 2ኛ |
| 184 | እንዳልካቸው በንቲ | ወንድ | ሒሳብ | 2ኛ |
| 185 | ጃፋር ምትኩ | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 186 | ጂላን ቃሲም | " | እንግሊዘኛ | 4ኛ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 187 | ክፍያለው | " | እንግሊዘኛ | 3ኛ |
| 188 | ከማል ጠሃ | " | ኮንስትራክሽን | 3ኛ |
| 189 | ቀነኒ ቀኖ | " | መካኒካል ኢንጅነሪንግ | 5ኛ |
| 190 | ቃሲም ሻፋ | " | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 191 | ቃሲም መሐመድ | ወንድ | ሒሳብ | 3ኛ |
| 192 | ከበደ ታምራት | " | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 193 | ቀበኔ ወንድሙ | ሴት | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 194 | ከድር የሱፍ | ወንድ | ታሪክ | 2ኛ |
| 195 | ካሳሁን ሺበሺ | " | መካኒካል ኢንጅነሪንግ | 3ኛ |
| 196 | ካሳሁን ጣሰው | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 197 | ክፍሉ አስቻለው | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 198 | ለታ ተስፋ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 2ኛ |
| 199 | ለባታ ፋፋ | " | ጂኦግራፊ | 2ኛ |
| 200 | ለገሰ ጀልቀባ | " | ፋርማሲ | 4ኛ |
| 201 | ልሊሴ ሰቦቃ | ሴት | አካል ማጎልመሻ | 2ኛ |
| 202 | ሌንጮ ጅራታ | ወንድ | ሶሲዮሎጂ | 3ኛ |
| 203 | ማሞ ሰቦቃ | " | ታሪክ | 2ኛ |
| 204 | ማርቆስ ዘላለም | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 4ኛ |
| 205 | ማቲዎስ ኮልፋሎ | " | ኢንፎርሜሽን ሳይንስ | 2ኛ |
| 206 | ምህረት ለሚ | ሴት | ቋንቋ | 3ኛ |
| 207 | መኮንን ኃይሉ | ወንድ | ታሪክ | 3ኛ |
| 208 | መለሰ አለማየሁ | " | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 209 | መንግሥቱ ደንጋ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 2ኛ |
| 210 | መርጋ | " | መካኒካል ኢንጅነሪንግ | 3ኛ |
| 211 | መርጋ ባንቲ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 212 | መርጋ በላይነህ | " | " | 3ኛ |
| 213 | መሠረት ፋንታሁን | " | ጂኦግራፊ | 2ኛ |
| 214 | መስከረም አያና | ወንድ | ሒሳብ | 4ኛ |
| 215 | ሚደቅሶ ጉደታ | " | ቋንቋ | 4ኛ |
| 216 | ሚላን ደርብ | " | ማኔጅመንት | 2ኛ |
| 217 | ሚራጅ አቡበከር | " | ቢውልዲንግ | 3ኛ |
| 218 | ሚርጊሴ ገመዳ | ሴት | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 219 | ምስጋናው አየለ | ወንድ | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 220 | ሞገስ ፋፋ | ወንድ | ቢዝነስ አዱኬሽን | 2ኛ |
| 221 | መሐመድ አ/ከድር | " | ቢውልዲንግ | 3ኛ |
| 222 | መሐመድ አብድርቃድር | " | ቢዝነስ ኡዱኬሽን | 2ኛ |
| 223 | መሐመድ አብዱራ | " | ማኔጅመንት | 2ኛ |
| 224 | መሐመድ አህመድ | " | ኢንፎርሜሽን ሳይንስ | 3ኛ |
| 225 | መሐመድ አሚን | " | " | 3ኛ |
| 226 | መሐመድ ሃይሌ | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 2ኛ |
| 227 | መሐመድ ሃሩን | " | ኬሚስትሪ | 2ኛ |
| 228 | መሐመድ ቀኖ | " | " | 3ኛ |
| 229 | መሐመድ እስማኤል | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 230 | መኮንን በዳዳ | " | ሶሲዮሎጂ | 3ኛ |
| 231 | መኮንን ገመቹ | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 2ኛ |
| 232 | መኮንን ኢፋ | " | - | - |
| 233 | መኮንን ታደሰ | " | ሶሲዮሎጂ | 4ኛ |
| 234 | መኮንን ታዬ | " | " | 3ኛ |
| 235 | ሞረዳ ከበደ | " | ጂኦግራፊ | 4ኛ |
| 236 | ሞቱማ ጋሪ | " | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 237 | ሙጉዳ ለሜሳ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 238 | ሙክታር ጀማል | ወንድ | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 239 | ሙሉጌታ መርጋ | " | - | - |
| 240 | ሙሉጌታ ንጉሴ | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 3ኛ |
| 241 | ሙሉነህ ታዬ | " | ታሪክ | 2ኛ |
| 242 | ሙሳ ዳውድ | " | ኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ | 4ኛ |
| 243 | ነጋሽ ሃይሉ | " | ታሪክ | 2ኛ |
| 244 | ነጋሽ ጥላሁን | " | " | 2ኛ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 245 | ነጋሽ ጥላሁን | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 2ኛ |
| 246 | ናሲሮ ሀሰን | " | ጂኦግራፊ | 4ኛ |
| 247 | ነዲ ሃጂ | ሴት | ፖለቲካል ሳይንስ | 2ኛ |
| 248 | ንጉሴ ለሜሳ | ወንድ | ሒሳብ | 3ኛ |
| 249 | ንጉሴ አመዩ | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 2ኛ |
| 250 | አብሳ አብደታ | " | ባዮሎጂ | 2ኛ |
| 251 | አላሚ ሳቀታ | " | - | - |
| 252 | ረቡማ | " | ሕግ | 5ኛ |
| 253 | ረታ ጎንፋ | " | ጂኦግራፊ | 2ኛ |
| 254 | ረታ በቀለ | " | ፊዝክስ | 3ኛ |
| 255 | ሮባ ገደፋ | " | ስታትስቲክስ | 3ኛ |
| 256 | ሰይድ መሐመድ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 257 | ሰርፈዲን ማማ | " | ስታትስቲክስ | 3ኛ |
| 258 | ሻራ ሃንጌባ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 259 | ሰይፈ ማማ | " | ታሪክ | 2ኛ |
| 260 | ሽምስዲን አብዱላሂ | " | ኬሚስትሪ | 2ኛ |
| 261 | ሻሾ ዘለቀ | " | " | 2ኛ |
| 262 | ሽብሩ ተሰፋዬ | " | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 263 | ሹሚ ቀኖ | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 264 | ስንቅነሽ አያና | ሴት | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 265 | ሲራጅ አ/ከድር | ወንድ | ሒሳብ | 3ኛ |
| 266 | ሲሳይ ባይሳ | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 267 | ሺዋዬ መርጋ | ሴት | " | 4ኛ |
| 268 | ሰለሞን ታደሰ | ወንድ | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 269 | ሱቱማ ቀነአ | " | ፖለቲካል ሳይንስ | 3ኛ |
| 270 | ታደሰ ከበደ | " | " " | 3ኛ |
| 271 | ታደሰ መገርሳ | " | " " | 4ኛ |
| 272 | ተፈሪ ፍሪሳ | " | ሕግ | 2ኛ |
| 273 | ጣሓ ደዲዮ | " | ጂኦሎጂ | 3ኛ |
| 274 | ጣሓ ጡሪ | " | ሕግ | 4ኛ |
| 275 | ታከለ ኃይሉ | " | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 276 | ታከለ ቶለሳ | " | ጂኦሎጂ | 3ኛ |
| 277 | ተኪቱ ምስጋና | ሴት | ታሪክ | 2ኛ |
| 278 | ታመነ በቀለ | ወንድ | ባዮሎጂ | 2ኛ |
| 279 | ታምራት አሰፋ | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 280 | ታምራት ጋዲሳ | " | ምሕንድስና | 2ኛ |
| 281 | ታምራት ተስፋዬ | " | ኬሚስትሪ | 3ኛ |
| 282 | ጠና አለማየሁ | " | ቲያትሪካል አርት | 2ኛ |
| 283 | ታሪኩ በየነ | " | አካውንቲንግ | 2ኛ |
| 284 | ታሪኩ ኢታና | " | ጂኦሎጂ | 4ኛ |
| 285 | ተሻለ ገላና | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 286 | ተሾመ ተስፋዬ | " | አካውንቲንግ | 2ኛ |
| 287 | ተፈራ አበራ | " | አካውንቲንግ | 2ኛ |
| 288 | ተክሉ በቀለ | " | አካል ማጎልመሻ | 2ኛ |
| 289 | ተመስገን እጀታ | " | ሒሳብ | 4ኛ |
| 290 | ጠና አለማየሁ | " | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 291 | ተስፋ ቀበታ | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 292 | ተስፋሁን ታደገ | " | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 293 | ተስፋዬ ዲሪባ | " | " | 2ኛ |
| 294 | ተስፋዬ ጉርሜሳ | " | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 295 | ተሰፋዬ ንጉሴ | " | ኬሚካል ኢንጅነሪንግ | 3ኛ |
| 296 | ተስፋዬ ሮባ | " | ቴክኖሎጂ | 4ኛ |
| 297 | ተሻለ ሹሚ | " | ጂኦሎጂ | 3ኛ |
| 298 | ተሾመ አመንቲ | " | ሳይኮሎጂ | 3ኛ |
| 299 | ተሾመ ዱጉማ | " | ጂኦግራፊ | 4ኛ |
| 300 | ተሰማ ደንጋሳ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 301 | ትዕግስት ሰለሞን | ሴት | ሳይኮሎጂ | 2ኛ |
| 302 | ትዕግስቱ በዳሳ | ወንድ | ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 303 | ጥላሁን ገመቹ | " | ጂኦግራፊ | 3ኛ |
| 304 | ቶሎሳ ደበላ | " | ፋርማሲ | 5ኛ |
| 305 | ቶሎሳ ሻንቆ | " | ኢኮኖሚክስ | 2ኛ |
| 306 | ቶማስ ብርሃኑ | " | ሒሳብ | 3ኛ |
| 307 | ሁሴን ያዶ | " | ሒሳብ | 4ኛ |
| 308 | ወዳጆ ታሪኩ | " | ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |
| 309 | ዋቀሳ ተሰማ | " | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 310 | ዋቅጋሪ ኤሊሳይ | " | " | 3ኛ |
| 311 | ዋቅጋሪ ሁንዴ | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 312 | ዋቅጋሪ ተመስገን | " | ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |
| 313 | ዋቅጋሪ ተሲሳ | " | እንግሊዘኛ | 2ኛ |
| 314 | ዋቅጋሪ ዩሐንስ | " | ቋንቋ | 2ኛ |
| 315 | ዋቆ ቀበታ | " | ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |
| 316 | ዋቅሹም ተረፈ | " | ባዮሎጂ | 4ኛ |
| 317 | ወንድሙ ፋንታ | " | ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |
| 318 | ወንድሙ ፍቃዱ | " | ቢዝነስ ኢዱኬሽን | 2ኛ |
| 319 | ወንድሙ ተስፋዬ | " | ታሪክ | 2ኛ |
| 320 | ወዳጆ ታሪኩ | " | ኢንጅነሪንግ | 2ኛ |
| 321 | ወርቅዓለም ሙለታ | ሴት | ሕግ | 3ኛ |
| 322 | ወርቅነሽ | " | ሶሲዮሎጂ | 3ኛ |
| 323 | ያደታ አብሳ | ወንድ | ኢንጅነሪንግ | 4ኛ |
| 324 | የታሪክ ስባቱ | ሴት | ሶሲዮሎጂ | 4ኛ |
| 325 | የዛብወርቅ መርጋ | " | እንግሊዘኛ | 4ኛ |
| 326 | ዮናስ ባጫ | ወንድ | ሶሲዮሎጂ | 2ኛ |
| 327 | የሱፍ ጡቄ | " | " | 3ኛ |
| 328 | ዛዬ ጨመራ | " | " | 4ኛ |
| 329 | ዘለቀ ሆልጅራ | " | እንግሊዘኛ | 3ኛ |
| 330 | ዘላለም አደሙ | " | " | 4ኛ |
| 331 | ስለሺ ደገፋ | " | ባዮሎጂ | 3ኛ |
| 332 | ተሾመ ቀበታ | " | ስታትስቲክስ | 3ኛ |
| 333 | ኤባ ሰንበታ | " | ሒሳብ | 2ኛ |
| 334 | ደረጀ ከበደ | " | ስታትስቲክስ | 3ኛ |

ማጠቃለያ

***የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በተማሪዎቹ ላይ የወሰዱት እርምጃ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉትን መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች የሚጥስ ነው፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18/1/ ላይ፡-***

> ***"ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡"***

**እንዲሁም በአንቀጽ 21/1/ ላይ፡-**

> ***"በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡"***

**በማለት የተደነገገውን በመጣስ ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱትን ድርጊቶች በተማሪዎቹ ላይ ፈጽመዋል፡፡ በተጨማሪ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30/1/ ላይ፡-**

> ***"ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ---"***

**በማለት የተደነገገውን በመጣስ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደርና ፖሊስ አቤቱታቸውን በሰላማዊ መንገድ ለማቅረብ የተሰባሰቡትን ተማሪዎች ታፍሰው እንዲወሰዱና እንግልትና ሥቃይ እንዲደርስባቸው አድርገዋል፡፡**

ከዚህ በተጨማሪ በፖሊስ ታፍሰው ከተወሰዱ በኋላ ክስ ሳይቀርብባቸውና አግባብ ያለው ምርመራ ሳይደረግባቸው ፖሊስ የለቀቃቸውን ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ለአንድ ዓመት ከትምህርት ማገዱና ጥፋት መሆኑ ባልተረጋገጠ ተግባር ይቅርታ መጠየቅን ወደ ትምህርት የመመለስ ቅድመ ሁኔታ ማድረጉ የተማሪዎቹን ሰብአዊ መብቶች በግልፅ የሚጋፋ ከመሆኑም በላይ ከአንድ አንጋፋ የትምህርት ተቋም የሚጠበቅ ተግባር አይደለም:: እንዲሁም በዩኒቨርሲተው ውስጥ ከተከሰተው ግጭት ጋር ተያይዞ በወንጀል ተጠርጥረው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የሚገኙትን 23 ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው እስከመጨረሻው ከትምህርት ማሰናበቱ በተማሪዎቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሰጥ ወንጀለኛ አድርጎ እንደመቁጠር ስለሆነና ይህ ደግሞ ሰዎች ከፍርድ በፊት ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት አላቸው የሚለውን ሕገ መንግሥታዊና ዓለማቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ የሚፃረር በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው::

ፖሊስ ተማሪዎቹን ከሕግ አግባብ ውጭ በቁጥጥር ሥር አውሎ፤ በተለይም ሌሊት ከተኙበት እየቀሰቀሰ ማሰሩ፣ ከዚህም አልፎ ታሳሪዎቹን ለፍርድ ማቅረብ ሲገባው ወደ ኮልፌ ፖሊስ ማሰልጠኛ ካምፕ በመውሰድ በረሃብና በዱላ መቅጣቱ፣ ዩኒቨርሲቲውም በግቢው ውስጥ የተፈጠሩትን አለመግባባቶች በውይይት ከመፍታት ይልቅ ተማሪዎቹን ለውጭ ኃይል አሳልፎ መስጠቱና ብዙ መጉላላት ደርሶባቸው የመጡትን ተማሪዎች ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ ማባረሩ በተማሪዎቹ ላይ የተፈጸመውን የመብት ረገጣ የከፋ ያደርገዋል:: ስለሆነም:

- ዩኒቨርሲቲው ከትምህርታቸው ያገዳቸው ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ፣
- በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የዋሉት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ተመልሰው ጉዳያቸው በአግባቡ በፍ/ቤት እንዲታይ፣
- በተማሪዎቹ ላይ ኢሰብአዊ በሆነ መልኩ ድብደባና የማሰቃየት ተግባር የፈጸሙት የጸጥታ ኃይሎች አባላት ለፍርድ እንዲቀርቡ፣

ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል::

ዜጎች እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍና ብሄራዊ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና የመንግሥታት ተወካዮች ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናትና አካላት በመጻፍ የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ ግፊት እንዲያደርጉ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል::

**ግልባጭ**

- ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት
  ፖ.ሣ.ቀ. 80001፣ ፋክስ (251-1) 55 09 00፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለፌዴሬሽን ምክር ቤት
  ፖ.ሣ.ቁ. 80001፣ የፋክስ ቁጥር (251-1) 55 07 22 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ፣ የኢፌዲሪ ፕሬዘዳንት
  ፖ.ሣ.ቁ 1031፣ ፋክስ (251-1) 55 20 20፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ፣ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር
  ፖሣ.ቁ. 1031፣ ፋክስ (251-1) 55 20 20፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለክቡር አቶ ሀርቃ ሀሮዬ፣ የኢፌዲሪ ፍትሕ ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁ. 1370፣ ፋክስ (251-1) 52 08 74 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለክብርት ወ/ሮ ገነት ዘውዴ፣ የትምህርት ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁ. 1367፣ ፋክስ (251-1) 55 02 99 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት
  ፖ.ሣ.ቁ.1176 ፣ ፋክስ (251-1) 550655 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ